DEPARTMENT OF HEALTH

# አብሮኝ የሚኖር ሰው በኮቪድ-19 ከታመመ ወደ ስራ መመለስ የምችለው መቼ ነው?ፅሁፍ

ከእኔ ጋር የሚኖር አንድ ሰው በኮቪድ-19 ታሟል። ወደ ሥራ መቼ መመለስ እችላለሁ? እርስዎ አብሮዎት የሚኖር ሰው በኮቪድ-19 የታመመ ከሆነ፣ ቤት ይቆዩ እንዲሁም ጤንነት ቢሰማዎትም ወይም ለኮቪድ-19 ተመርምረው ነጋትቭ ቢሆንም እንኳ እነዚህን መመሪያዎች ይከተሉ።

ለተቆጣጣሪዎ ያሳውቁ እና ከቻሉ ከቤት ይስሩ። በወሳኝ መሰረተ ልማት ውስጥ የሚሰሩ ከሆነ እና የእርስዎ መቅረት የሰራተኛ ቀውስ የሚፈጥር ከሆነ፣ ወደ ሥራ መሄድ ይችሉ ይሆናል ነገር ግን፤ ጭንብል ይልበሱ እና ከስራ ባልደረቦችዎ እና ከጎብኝዎች 6 ጫማ (2 ሜትር) ርቀው ይቆዩ።

በቤት፣ ከታመመ የቤተሰብዎ አባል እራስዎን ይለዩ፣ እና እንደ የቤት መገልገያዎች ወይም ስልኮች ያሉ ምንም አይነት ነገሮችን ለ14 ቀናት አያጋሩ። ከ14 ቀናት በኋላ፣ እንደተለመደው ወደ ሥራዎ መመለስ ይችላሉ።

የታመሙ የቤተሰብ አባላት እስኪሻላቸው ድረስ  እና እነዚህ ነገሮች ሁሉ እውነት እስኪሆኑ ድረስ እራስዎን ማግለልዎን ይቀጥሉ፡-

1. የሕመማቸው ምልክቶች፣ እንደ ሳል ወይም የትንፋሽ ማጠር፣ ተሻሽለዋል።
2. የሕመማቸው ምልክቶች ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ ቢያንስ 10 ቀናት ሆነዋል።
3. ያለ ትኩሳት መቀነሻ መድሃኒት፣ ትኩሳት ሳይኖራቸው ለ 24 ሰዓታት ቆይተዋል።

እራስዎን ከታመመ የቤተሰብዎ አባል መለየት ካልቻሉ። ቤትዎ ለምን ያህል ጊዜ መቆየት እንዳለብዎ ለመወያየት፣ ከእርስዎ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሐኪምዎን፣ ክሊኒክዎን ወይም የህዝብ ጤና ባለሙያዎን ያነጋግሩ። በአጠቃላይ፣ የታመመው የቤተሰብ አባል እስከሚሻለው እና ከዚያ በኋላ ተጨማሪ እስከ 14 ቀናት ድረስ ቤት መቆየት ይችላሉ።

በኮቪድ-19 የሕመም ምልክቶች የታመሙ ከሆነ፣ ለመመርመር ሐኪምዎን ወይም የአካባቢዎን ክሊኒክ ያነጋግሩ። እንደ ታመመው የቤተሰብዎ አባል፣ የሕመምዎ ምልክቶች እስኪሻሻሉ፣ የሕመምዎ ምልክቶች ከጀመሩ ቢያንስ 10 ቀናት እስከሚሆን፣ እናም ያለ ትኩሳት መቀነሻ መድሃኒት ትኩሳት ሳይኖርዎት 24 ሰዓታት እስከሚሆንዎት ድረስ፣ በቤት ይቆዩ።

ስለ ኮቪድ-19 ላይ ወቅታዊ መረጃን ለማግኘት health.mn.gov ን ይጎብኙ

Minnesota Department of Health
Communications Office
PO Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
651-201-4989
health.communications@state.mn.us
www.health.state.mn.us

08/10/20

When Can I Return to Work if Someone Living With Me is Sick With COVID-19? (Amharic)

To obtain this information in a different format, call: 651-201-4989